# <u>የግልግል ዳኝነት እና የዕርቅ አሰራርን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር----/2011</u>

የማኅበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊ፣ የንግድ፣ የኢንቨስትመንት እና የመሳሰሉት አለመግባባቶችን በግልግል ዳኝነትና በዕርቅ መፍታት አስፈላጊ በመሆኑ ፤

የፍርድ ቤቶችን ጫና፣ የጊዜ መጓተት፣ ተገቢ ያልሆነ ወጪ ለማስቀረት እና የተከራካሪ ወገኖችን ሕጋዊ መብትና ጥቅም ለመጠበቅ አለመግባባቶችን በአማራጭ የዳኝነት ሥርዓት መፍታት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የግልግል ዳኝነትና ዕርቅ ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻውንና ዓለም ዓቀፍ የግልግል ዳኝነት ስምምነቶች ተግባራዊ ለማድረግ እንዲሁም ለነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ማደግ አስተዋጽዖ የሚያደርግ በመሆኑ፤

በውጭ ሀገር ለተሰጡ የግልግል ዳኝነት ፍርዶች እውቅና መስጠት እና ማስፈፀም አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) እና (6) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

### 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የግልግል ዳኝነት እና የዕርቅ አዋጅ ቁጥር ---/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "የግልግል ዳኝነት ውሳኔ" ማለት አለመግባባቶችን ለመፍታት በቋሚነት በተደራጀ የግልግል ተቋም ወይም በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት በጊዜያዊነት በሚቋቋም የግልግል አካል የሚሰጥ ዳኝነት ነው፡፡
2. "የግልግል ስምምነት" ማለት ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸው ካለው ውል ወይም ውል ካልሆነ ግንኙነት የተፈጠረውን ወይም ሊፈጠር የሚችለውን አለመግባባት በሙሉ ወይም በከፊል በግልግል ዳኝነት ለመፍታት በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴዎች አማካኝነት የሚያደርጉት ስምምነት ወይም በውል ውስጥ የሚያካትቱት የግልግል አንቀጽ ነው፡፡
3. "በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የተደረገ ውል" ማለት በመረጃ መረብ ሥርዓት አማካኝነት የሚደረግ ስምምነት ሆኖ በኢሜይል፣ በቴሌግራፍ፣ በቴሌክስ እና ሌሎች መሰል መገናኛ ዘዴዎች የሚደረግ ስምምነትን ያካትታል፡፡
4. "ዕርቅ" ማለት ሽምግልና፣ ዕርቅ ወይም ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጥበትን ሂደት የሚያካትት ሆኖ፤ ዓላማው ዘላቂ መግባባት ላይ ለመድረስ በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት አለመግባባቱ እንዲፈታ ለማስቻል በሚሰየም ሦስተኛ ወገን አማካኝነት የሚደረግ ሂደት ነው፡፡

5. “የግልግል ዳኝነት ማዕከል” ማለት መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ የግልግል ማዕከል ነው፡፡
6. “ፍርድ ቤት” ማለት ለግልግል ዳኝነት በቀረበው ጉዳይ ላይ የሥረ ነገር ሥልጣን ያለውና ክስ ቢቀርብ ኖሮ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው የፌደራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ነው፡፡
7. “የግልግል ዳኝነት ጉባዔ” ማለት አንድ ዳኛ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ዳኞች የሚሰየሙበት ስብስብ ማለት ነው።
8. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
9. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

**3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ አዋጅ በግልግል ዳኝነት ፣ በዕርቅ በሚታዩ ጉዳዮች እንዲሁም እውቅና ባገኙ የዓለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**4. <u>መርህ</u>**

1. በሕግ በግልጽ በተከለከሉ ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር፣ ተዋዋይ ወገኖች አለመግባባቶቻቸውን ለመፍታት የግልግል ስምምነቶች ማድረግ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አዋጅ ልዩ ክፍል በግልጽ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች በሕጉ ጠቅላላ መርህ መሠረት ይተረጎማሉ፡፡

**5. <u>የፍርድ ቤት ጣልቃ ገብነት</u>**

ፍርድ ቤቶች በዚህ አዋጅ ተለይቶ ከተሰጣቸው ሥልጣን በስተቀር፣ በዚህ አዋጅ በተደነገጉ በማናቸውም ጉዳይ ላይ ጣልቃ አይገቡም፡፡

**6. <u>ለግልግል የማይቀርቡ ጉዳዮች</u>**

የሚከተሉት አለመግባባቶች ለግልግል ዳኝነት አይቀርቡም፡፡

1. የጋብቻ፣ የጉዲፈቻ፣ የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት እና የውርስ ጉዳዮች፣
2. በሕግ ለሚመለከታቸው አስተዳደራዊ አካላት በተሰጠ ሥልጣን ሥር የሚሸፈኑ አስተዳደራዊ አለመግባባቶች፣
3. የወንጀል ጉዳዮች፣

4. በግልግል እንዳይታዩ በሕግ የተከለከሉ ሌሎች ጉዳዮች፡፡

## 7. በግልግል ዳኝነት ተፈፃሚ ስለሚሆኑ ሕጎች

1. ለግልግል የሚቀርቡ ተዋዋይ ወገኖች በዚህ አዋጅ መሠረት ለመገላገል እንደተስማሙ ይቆጠራል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም፣ ተዋዋይ ወገኖች የተስማሙበት ሌላ የግልግል ሕግ ወይም የዚህን አዋጅ አንቀጾች በማሻሻል ያደረጉት ስምምነት ያለ እንደሆነ የተዋዋይ ወገኖቹ ስምምነት የፀና ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም ፣ስምምነቱን በራሱ ለመፈጸም የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ወይም ግልግሉ የሚታይበትን ሀገር ሕግ አስገዳጅ ድንጋጌዎች የሚጻረር ሲሆን ወይም ይህን አዋጅ የሚቃረን ሲሆን የተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ተፈጻሚ ሊሆን የማይችል የተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ሲያጋጥም በተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ ለዚህ አዋጅ ተስማሚ በሆነ ሌላ የግልግል ሕግ ወይም በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ግልግሉ ይታያል፡፡

## 8. የግልግል ስምምነት ቅርፅና ይዘት

1. የግልግል ስምምነት በጽሑፍ መሆን አለበት፡፡
2. የግልግል ስምምነት በጽሑፍ ተደርጓል የሚባለው፡-

**ሀ/** ስምምነቱ በቃል፣ በአድራጎት ወይም በሌላ በማናቸውም መገናኛ ዘዴ ቢደረግም ይዘቱ በጽሑፍ ሰፍሮ ሲገኝ፣

**ለ/** በኤሌክትሮኒክ መገናኛ ዘዴ የተደረገ የግልግል ስምምነት መረጃው በተፈለገ ጊዜ ጥቅም ላይ ለማዋል ተደራሽ ሆኖ ሲገኝ፣

**ሐ/** በግልግሉ ሂደት አንደኛው ተዋዋይ ወገን የስምምነቱን መኖር ከገለፀ እና በሌላው ተዋዋይ ወገን የስምምነቱ መኖር በ 15 ቀናት ካልተካደ፣

**መ/** አስቀድሞ የተደረገን የግልግል ውል የሚያጣቅስ ማንኛውም ውል ሲኖር ማጣቀሱ የተደረገበት ምክንያት የግልግሉን ስምምነት የውሉ ክፍል ለማድረግ ሲሆን፣

ነው፡፡

## 9. የግልግል አንቀጽ

1. የግልግል አንቀጽ የሚባለው አንድ የውል ግንኙነት የመሠረቱ ተዋዋዮች ከውሉ የሚነሱና ከውሉም ጋር የተያያዙ አለመግባባቶች በግልግል ዳኝነት እንዲፈቱ በመስማማት በአንድ ውል ውስጥ በጽሑፍ የሚገልጹት የግልግል ቃል ነው፡፡
2. በውል ስምምነት ውስጥ የተካተተ የግልግል አንቀጽ ከሌሎቹ የውል አንቀጾች የተለየና ራሱን የቻለ ስምምነት እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

3. ተዋዋይ ወገኖች በተቃራኒው ካልተዋዋሉ በስተቀር በዋናው ውል ላይ የሚደረግ የማሻሻል፣ የመለወጥ፣ የማቋረጥ ወይም የመሻር ስምምነት ፣ የግልግል አንቀጹን ዋጋ አያሳጣውም፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ ግልግል ዳኝነት ማዕከል

## ንዑስ ክፍል አንድ

## መንግሥታዊ የግልግል ዳኝነት ማዕከል

**10. መቋቋም**

1. የአዲስ አበባ አለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ማዕከል (ከዚህ በኋላ “ማዕከል” ተብሎ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

2. የማዕከሉ ተጠሪነት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት ይሆናል፡፡

**11. ዋና መሥሪያ ቤት**

የማዕከሉ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስአበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል፡፡

**12. የማዕከሉ ሥልጣንና ተግባር**

ማዕከሉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የግልግል ዳኝነት ጉዳዮችን በሚመለከት በአስተዳደራዊ ተቋምነት ያገለግላል፡፡
2. አማራጭ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በጥናት ይለያል፣ ያስተዋውቃል፣ያሰራጫል፡፡
3. የግልግል ዳኝነት አገልግሎትን ይሰጣል፤
4. ማዕከሉ ተመራጭ የግልግል ዳኝነት ማዕከል እንዲሆን ይሠራል፣ ያስተዋውቃል፡፡
5. መንግሥታዊ ያልሆኑ የግልግል ማዕላትን ይመዘግባል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፡፡
6. በስሙ ንብረት ያፈራል፣ይከሳል፣ይከሰሳል፡፡

**13. የማዕከሉ አቋም**

ማዕከሉ፡-

1. ቦርድ፣

2. ዳይሬክተር ፣

3. ሌሎች አስፈላጊ ሰራተኞች፣

ይኖሩታል፡፡

**14. <u>የቦርድ አባላት</u>**

1. ቦርዱ በመንግሥት የሚሾሙ ሰብሳቢውን ጨምሮ ሰባት አባላት ይኖሩታል፡፡
2. በመንግሥት የሚሾሙት የቦርድ አባላት ከመንግሥት ተቋማት ውጭ ከሚሠሩ ባለሙያዎች መሆን አለባቸው፡፡
3. የቦርድ አባላቱ የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ነው፡፡

**15. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ቦርዱ ፡-

1. ማዕከሉን በበላይነት ይመራል፡፡

2. የማዕከሉን የሥራና የበጀት እቅድ አፈፃፀም ይከታተላል፡፡

3. የማዕከሉን ዳይሬክተር ይሾማል፡፡

4. የማዕከሉን አሠራር በተመለከተ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

**16. <u>የዳይሬክተሩ ሥልጣን እና ተግባር</u>**

ዳይሬክተሩ፡-

1. ማዕከሉን ይመራል፣ያስተዳድራል፡፡
2. ለማዕከሉ በተፈቀደው በጀት መሠረት የፋይናንስ ጉዳዮችን ያስተዳድራል፡፡
3. ለማዕከሉ የሚያስፈልጉ ሠራተኞችን በመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳራል፣ ከሥራ ያሰናብታል፡፡
4. በማንኛውም ጉዳይ ማዕከሉን ይወከላል፡፡
5. ማንኛውም አካል የሚልከውን የግልግል ዳኝነት ስምምነት ይቀበላል፣ ያስተዳድራል፡፡

**17. <u>በጀት</u>**

ማዕከሉ በመንግሥት በጀት፣ ለአገልግሎት በሚከፈል ክፍያ እና በእርዳታ በሚገኝ ገቢ ይንቀሳቀሳል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## መንግሥታዊ ያልሆነ የግልግል ዳኝነት ማዕከል

**18. ሌሎች የግልግል ዳኝነት ማዕከላት በኢትዮጵያ**

ይህ አዋጅ ነባር የግልግል ዳኝነት ተቋማት እንዳይቀጥሉም ሆነ አዳዲስ እንዳይቋቋሙ አይከለክልም፡፡

**19. መንግሥታዊ ያልሆነ የግልግል ማዕከል ስለመመሥረት**

1. ለትርፍ የሚሠሩ ብሔራዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ የግልግል ማዕከላት ሊመሠረቱ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚመሠረት የግልግል ማዕከል በማዕከሉ ተመዝግቦ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
3. የግልግል ዳኝነት ማዕከል ፈቃድ በየዓመቱ መታደስ ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም አግባብ ባለው ሕግ የተፈቀደላቸው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አስፈላጊውን መስፈርት አሟልተው የግልግል ዳኝነት አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፡፡
5. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) እና (3) የተደነገጉት ቢኖሩም ተዋዋይ ወገኖች እንደአስፈላጊነቱ በሚያቋቁሙት ጊዜያዊ የግልግል አካል፣ የግልግል ዳኝነት ሊሰጥ ይችላል፡፡

**20. የግልግል ማዕከል ለመመሥረት መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች**

ማንኛውንም የግልግል ማዕከል መመሥረት የሚቻለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው፡፡

1. የማዕከል ስም፣ አድራሻ ፣ የመተዳደሪያ ደንብ እና የመመሥረቻ ጽሑፍ፣
2. ለሥራ አስፈላጊ የሆነ ንብረት፣
3. በማዕከሉ የተመዘገቡ የግልግል ዳኝነት ባለሙያዎች፡፡

## ክፍል ሦስት

## የግልግል ማዕከላት ሊመሩባቸው የሚገቡ መሠረታዊ መርሆች

**21. መረጃዎችን ስለመስጠት**

ማንኛውም የግልግል ማዕከል ለተገልጋይ ወይም ለጠየቀ አካል በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ግልጽ እና ትክክለኛ መረጃ መስጠት አለበት፡፡

1. የግልግል ማዕከሉን አደረጃጀት፣ አገልግሎቶች፣ አሠራርና እና ክፍያ፣

2. በግልግል ማዕከሉ እና አብረውት በሚሠሩ ሌሎች ገለልተኛ አካላት መካከል ሊኖር የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ፣ ሕጋዊ፣ ሙያዊ ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ግንኙነቶች፣

3. ተቋማዊና የግል ግጭት ሲያጋጥም ለመፍታት ስለሚወሰዱ የጥንቃቄ ርምጃዎች እንዲሁም ገለልተኛ አካላት እና የግልግል ማዕከሉ የሚመሩባቸው የሥነ ምግባር ደንቦች፣

4. ከግልግል ማዕከሉ ጋር አብረው የሚሠሩ ገለልተኞች ስለሚመረጡበት መንገድ፣ ሊኖራቸው ስለሚገባ ሥልጠና እና የሙያ ብቃት እንዲሁም አብረው ለመሥራት የሚፈልጉ ሌሎች ገለልተኛ አካላት ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶች፣

**22.**<u>ተከራካሪ ወገኖችን በእኩል ስለማስተናገድ</u>

ሁለቱም ወገኖች በእኩል ሊስተናገዱ ይገባል፡፡ እያንዳንዱ ወገን ጉዳዩን ለማቅረብ ሙሉ እድል ማግኘት አለበት፡፡

**23.** <u>ፍትሐዊነት እና ገለልተኝነት</u>

ማንኛውም የግልግል ማዕከል የሚሰጠው አገልግሎት ፍትሐዊና ገለልተኛ መሆን አለበት፡፡

**24.** <u>ድጋፍ ስለመስጠት</u>

ማንኛውም የግልግል ማዕከል የሰው ኃይሉን እና ሀብቱን ግምት ውስጥ በማስገባት ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች በዝቅተኛ ክፍያ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ያለክፍያ አገልግሎት መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

**25.** <u>የጥቅም ግጭት</u>

1. ማንኛውም የግልግል ማዕከል በገለልተኝነቱ እና በነፃነቱ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር የሚችልን ወይም ለአንደኛው ወገን ሊያደላ የሚያስችል ሁኔታን የሚፈጥር ጥቅም ወይም ግንኙነት መኖሩን ለተዋዋይ ወገኖች ማሳወቅ አለበት፡፡
2. በውል ወይም በሕግ በሌላ አኳኋን የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ሁኔታው የተገለጸላቸው ሁሉም ተዋዋይ ወገኖች ጉዳያቸው በግልግል ማዕከሉ እንዲታይላቸው ፍላጎታቸውን ካልገለጹ በቀር የግልግል ማዕከሉ አገልግሎት መስጠቱን ማቆም አለበት፡፡

**26.** <u>ስለ ቅሬታ አቀራረብ</u>

ማንኛውም የግልግል ማዕከል፡-

1. በአስተዳደሩ ወይም በገለልተኛ አካል በተሰጠው አገልግሎት ላይ ያለውን የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት ለተዋዋይ ወገኖች በግልጽ፣ በትክክለኛ እና ለመረዳት በሚያስችል መንገድ ማሳወቅ፣

2. ቅሬታ የቀረበበትን ገለልተኛ አካል ወይም ሌላ ግለሰብ ጉዳዩን ፍትሐዊና ገለልተኛ በሆነ መንገድ ለማጣራት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት፣

ይኖርበታል፡፡

**27. <u>ምስጢራዊነት</u>**

በሕግ ወይም በስምምነት በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር፣ የግልግል ዳኝነት ማዕከላት እና የማናቸውም ግልግል ጉባዔ የሥራ ሂደት ምስጢራዊነት መጠበቅ አለበት፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ስለ ግልግል ዳኞች ብዛት እና አሰያየም</u>

**28. <u>የግልግል ዳኞች ብዛት</u>**

1. ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኞቹን ብዛት በስምምነት መወሰን ይችላሉ፡፡ሆኖም የዳኞቹ ብዛት ጎደሎ ቁጥር መሆን አለበት፡፡
2. ተዋዋይ ወገኖች የዳኞችን ብዛት በስምምነት መወሰን ያልቻሉ እንደሆነ የግልግል ዳኞች ብዛት ሦስት ይሆናል፡፡

**29. <u>የግልግል ዳኞችን ስለመሰየም</u>**

1. ተዋዋይ ወገኖች በሌላ መንገድ ካልተስማሙ በስተቀር፣ማንኛውም ሰው በዜግነቱ ምክንያት የግልግል ዳኛ ከመሆን ሊታገድ አይችልም፡፡
2. በዚህ አዋጅ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ተዋዋይ ወገኖች በግልግል ዳኞች አሰያየም ሥነ ሥርዓት ላይ የመስማማት ነፃነት አላቸው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ተዋዋይ ወገኖች ያልተስማሙ እንደሆነ፣ የሚከተለው ተፈፃሚ ይደረጋል፡፡

**ሀ/** ሦስት ዳኞች ያሉበት የግልግል ዳኝነት ላይ እያንዳንዱ ወገን አንድ ዳኛ ይመርጣል፤ሁለቱ የተመረጡ ዳኞች በሰብሳቢነት የሚሠራውን ሦስተኛ ዳኛ ይመርጣሉ፡፡

**ለ/** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(ሀ) የተደነገገው ቢኖርም፣ አንደኛው ወገን ዳኛ እንዲመርጥ በሌላኛው ወገን በተጠየቀ በሠላሳ ቀናት ውስጥ ዳኛ መምረጥ ካልቻለ ወይም ሁለቱም ዳኞች ከተመረጡ በሠላሳ ቀናት

ውስጥ ሦስተኛ ዳኛ መምረጥ ላይ መስማማት ካልቻሉ፤በአንደኛው ወገን ጠያቂነት የማዕከሉ ኃላፊ ይሰይማል፡፡

**ሐ/** አንድ ዳኛ ብቻ ባለበት የግልግል ዳኝነት ሁለቱም ወገኖች መስማማት ያልቻሉ እንደሆነ በ30 ቀናት ውስጥ ዳኛ እንዲሰይምላቸው ለማዕከሉ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

4. ተዋዋይ ወገኖች በተስማሙበት ዳኛን የመምረጥ ሂደት መሠረት፡-

**ሀ/** አንደኛው ወገን በስምምነቱ የሚጠበቅበትን መወጣት ካልቻለ፣ወይም

**ለ/** ተዋዋይ ወገኖች ወይም ሁለቱም ዳኞች በስምምነቱ ከሚጠበቅባቸው መግባባት ላይ መድረስ ካልቻሉ፣ወይም

**ሐ/** ተቋምን ጨምሮ ሦስተኛ ወገን በስምምነቱ ላይ የተጣለበትን ኃላፊነት መወጣት ካልቻለ፣ በሁለቱም ወገኖች የተደረሰው ዳኛን የመምረጥ ስምምነት ሌላ ዳኛ የሚመረጥበትን መንገድ ካላስቀመጠ በቀር ማንኛውም ወገን አስፈላጊው ርምጃ እንዲወሰድ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 ወይም 4 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ማዕከሉ የሚሰጠው ውሳኔ ይግባኝ አይቀርብበትም፡፡
6. ማዕከሉ ዳኛ በሚመርጥበት ጊዜ በስምምነቱ የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎችንና ዳኛው ገለልተኛ እና ነፃ መሆኑን የሚያረጋግጡ መስፈርቶችን ከግምት ማስገባት አለበት፡፡
7. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩ የሚታየው በአንድ ዳኛ ብቻ በሚሆንበት ጊዜ ከላይ ከተገለፁት በተጨማሪ የግልግል ዳኛው ዜግነት ከተዋዋይ ወገኖች የተለየ ስለመሆኑ ከግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡

**30. <u>የግልግል ዳኞችን ስለመቃወም</u>**

1. ማንኛውም ሰው ዳኛ እንዲሆን ጥያቄ ሲቀርብለት ወይም ከተመረጠ ገለልተኛነቱን እና ነፃነቱን ጥርጣሬ ውስጥ የሚከት ማንኛውንም ዓይነት ሁኔታ አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. የአንድን ዳኛ መመረጥ መቃወም የሚቻለው ገለልተኛነቱን እና ነፃነቱን አሳማኝ ጥርጣሬ ውስጥ የሚከቱ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ወይም በግልግል ስምምነቱ ላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን የማያሟላ ሲሆን ብቻ ነው፡፡
3. አንድ ወገን ራሱ በመረጠው ዳኛ ላይ ወይም በምርጫው ሂደት በተሳተፈበት ዳኛ ላይ ተቃውሞ ማቅረብ የሚችለው ዳኛው ከተመረጠ በኋላ በሚያውቀው ምክንያት ብቻ ነው፡፡

**31. <u>የተቃውሞ ሥነ ሥርዐት</u>**

1. በዚህ አዋጅ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር፣ ተዋዋይ ወገኖች ተቃውሞ በሚቀርብበት ሥነ ሥርዓት ላይ ስምምነት ማድረግ ይችላሉ፡፡
2. በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ ስምምነት የሌለ እንደሆነ በግልግል ዳኛ ላይ ተቃውሞ የማቅረብ ፍላጐት ያለው ወገን የግልግል ዳኛው ከተሰየመበት ወይም ለተቃውሞ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ካወቀበት ጊዜ አንስቶ በሚቆጠሩ አሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ለጉባዔው በጽሑፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

3. ተቃውሞ የቀረበበት ዳኛ በራሱ ፈቃድ ካልተነሳ ወይም ሌላኛው ወገን በተቃውሞው ካልተስማማ በስተቀር፣ ተቃውሞ ያልተነሳባቸው ዳኞች ተቃውሞው ላይ ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡ እኩል ድምፅ በሚኖርበት ጊዜ የጉባዔው ሰብሳቢ ያለበት ሀሳብ የጉባዔው ውሳኔ ይሆናል፡፡
4. ጉዳዩ እየታየ ያለው በአንድ ዳኛ ከሆነ እና ዳኛው ላይ ተቃውሞ ከተነሳ የማዕከሉ ኃላፊ ተቃውሞውን ዐይቶ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
5. በሁለቱም ወገኖች የግልግል ስምምነት ወይም በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የቀረበ ተቃውሞው ውድቅ የተደረገበት ሰው ውጤቱ በተነገረው በሠላሳ ቀናት ውስጥ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ ይግባኝ አይቀርብበትም፡፡
6. ፍርድ ቤት በተቃውሞው ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የግልግል ዳኝነት ሂደቱ ታግዶ ይቆያል፡፡

## 32. <u>ሥራን በአግባቡ ማከናወን አለመቻል</u>

1. አንድ ዳኛ በሕግ ወይም በሁኔታዎች ምክንያት ሥራውን በአግባቡ ማከናወን ካልቻለ ከኃላፊነቱ ይነሳል፡፡ ሆኖም እነዚህ ሁኔታዎች ስለመኖራቸው አከራካሪ ሆኖ ሲገኝ ማንኛውም ወገን ለማዕከሉ ማመልከት ይችላል፡፡
2. በማዕከሉ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ለፍርድቤት ማመልከት ይችላል፡፡ ፍርድቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ ይግባኝ አይቀርብበትም፡፡
3. በዚህ አንቀፅ መሠረት አንድ ዳኛ ሥልጣኑን መልቀቁ ወይም እንዲለቅ ተዋዋይ ወገኖች መስማማታቸው በዚህ አዋጅ አንቀፅ 30/2/ የተቀመጡ ሁኔታዎችን መቀበሉን አያሳይም፡፡

## 33. <u>ተተኪ ዳኛ ስለመሰየም</u>

አንድ የግልግል ዳኛ በማንኛውም ምክንያት ከጉባዔ እንዲነሳ በመወሰኑ ወይም ራሱ ሥራውን በማቋረጡ ከኃላፊነቱ ሲሰናበት በምትኩ ሌላ ዳኛ ይሰየማል፡፡ አዲሱ የግልግል ዳኛ የሚሰየመው የተቀየረው ዳኛ በተሰየመበት ሥርዓት መሠረት ነው፡፡

# <u>ክፍል አምስት</u>

# <u>ስለ ግልግል ዳኝነት ጉባዔ</u>

## 34. <u>የግልግል ዳኝነት ጉባዔ የሥረ ነገር ክርክር ሥልጣን</u>

የግልግል ዳኝነት ጉባዔው አንድን ጉዳይ የማየት ሥልጣን አለኝ ወይስ የለኝም በሚለው ላይ እንዲሁም የግልግል ዳኝነት በተዋዋይ ወገኖች ውስጥ ስምምነት ስለመኖሩ እና ስምምነቱም የፀና ስለመሆኑ የመወሰን ሥልጣን አለው፡፡

## 35. <u>በግልግል ጉባዔ የሥረ ነገር ሥልጣን ላይ ስለሚቀርብ ተቃውሞ</u>

1. በግልግል ጉባዔ የሥረ ነገር ሥልጣን ላይ የሚነሳ ተቃውሞ ጉባዔው በፍሬ ነገር ላይ የሚያደርገውን ክርክር ከመስማቱ በፊት በመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞ መቅረብ አለበት፡፡
2. በግልግል ጉባዔው በመታየት ላይ ያለው ጉዳይ ከግልግል ጉባዔው የሥረ ነገር ሥልጣን በላይ ነው የሚል ተቃውሞ መቅረብ የሚገባው ጉዳዩ እንደተጀመረ መሆን አለበት፡፡
3. የግልግል ጉባዔ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም 2 ከተደነገገው ጊዜ ዘግይቶ የቀረበ ተቃውሞ መቅረብ ያልቻለበት ምክንያት በቂ መሆኑን የተረዳው እንደሆነ ሊቀበለው ይችላል፡፡
4. በግልግል ጉባዔው የሥረ ነገር ክርክር ሥልጣን ላይ የቀረበው ተቃውሞ በጉባዔው ተቀባይነት ካገኘ እና ጉባዔው በሥልጣኑ ወሰን ላይ የመወሰን ሥልጣን ያለው ሲሆን፡-

   **ሀ/** በጉባዔው ሥልጣን ወሰን ላይ የቀረበ ተቃውሞ እንደሆነ ጉባዔው ውሳኔ ይሰጣል፡፡

   **ለ/** የቀረበው ተቃውሞ በሥረ ነገር ክርክር ላይ ሲሆን ጉባዔው በፍሬ ነገር ላይ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ አያይዞ ሊወስን ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው ቢኖርም፣ ተዋዋይ ወገኖች ለግልግል ጉባዔው በቀረበው ተቃውሞ አወሳሰን ላይ ያደረጉት ስምምነት ሲኖር ጉባዔው በስምምነቱ መሠረት ይወስናል፡፡
6. በግልግል ጉባዔ የሥረ ነገር ሥልጣን ወሰን ላይ ተቃውሞ ለፍርድ ቤት የቀረበ እንደሆነ ጉባዔው በሂደት ላይ ያለውን የግልግል ዳኝነት ሂደት ማስቀጠል እና ውሳኔ መስጠት አይችልም፡፡

**36.** <u>**የሥነ ሥርዓት ሕግ ስለመወሰን**</u>

1. በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ሊከተለው የሚገባውን የሥነ ሥርዓት ሕግ በስምምነት ሊወስኑ ይችላሉ፡፡
2. ተዋዋይ ወገኖች በስምምነት የሥነሥርዓት ሕጉን ካልወሰኑ ጉባዔው ተገቢ ነው ብሎ ያሰበውን ሥነ ሥርዐት ሊከተል ይችላል፡፡ ለግልግል ዳኝነት ጉባዔው የተሰጠው ሥልጣን የማስረጃ ተቀባይነት፣አስፈላጊነት እና ምዘና ላይ ለመወሰን የተሰጠውን ሥልጣንም ይጨምራል፡፡

**37.** <u>**የግልግል ዳኝነት ጉባዔ መቀመጫ ቦታ**</u>

1. ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኝነት የሚካሄድበትን ቦታ መምረጥ ይችላሉ፡፡
2. ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኝነት የሚካሄድበትን ቦታ በስምምነት መምረጥ ካልቻሉ፣ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ለተከራካሪ ወገኖች አመቺነቱንና ሌሎች ሁኔታዎችን ከግምት በማስገባት ቦታውን መወሰን አለበት፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ቢኖሩም ተዋዋይ ወገኖች በሌላ መንገድ ካልተስማሙ በስተቀር ለምክክር፣ የምስክርን ቃል ለመስማት፣ የባለሙያዎችን ቃል ለመቀበል፣ ንብረቶች እና ሰነዶችን ለመፈተሽ ሲባል የጉባዔው ዳኞች በሌላ ቦታ ሊገናኙ ይችላሉ፡፡

## 38. የግልግል ዳኝነት ሂደት ስለመጀመር

ተዋዋይ ወገኖች በሌላ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር የግልግል ዳኝነት ሂደቱ የተጀመረበት ቀን ተብሎ የሚታሰበው ከሳሽ ክርክሩን ለግልግል ዳኝነት ለመምራት እንደወሰነ የሚገልፅ ጥያቄ ለተከሳሽ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡

## 39. ቋንቋ

1. በግልግል ዳኝነት ሂደት ስለሚጠቀሙበት ቋንቋ ተዋዋይ ወገኖች በስምምነት ሊወስኑ ይችላሉ፡፡
2. ተዋዋይ ወገኖች በቋንቋ ምርጫ መስማማት ካልቻሉ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው የግልግል ዳኝነት የሚካሄድበትን ቋንቋ ሊወስን ይችላል፡፡
3. የግልግል ዳኝነት ጉባዔው የሰነድ ማስረጃዎች በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት መሠረት በተመረጠው ቋንቋ ወይም በተመረጡት ቋንቋዎች ተተርጉሞ እንዲቀርብ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ማዘዝ ይችላል፡፡
4. ተዋዋይ ወገኖች ያደረጉት የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የግልግል ዳኝነት ጉባዔውን የሥራ ቋንቋ ለማይችል ተዋዋይ ወገን፣ ምስክር ወይም ኤክስፐርት ተርጓሚ ይመድብለታል፡፡

## 40. ጊዜያዊ የመጠበቂያ ርምጃዎች

1. ከተከራካሪ ወገኖች በአንዱ የሚቀርብለትን ጥያቄ መነሻ በማድረግ፣ በግልግል ዳኝነት እየታየ ያለውን ክርክር የሚመለከቱ ጊዜያዊ የመጠበቂያ ርምጃዎች መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው፣ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው የዚህን ዓይነት ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2. ጊዜያዊ የመጠበቂያ ርምጃው የክርክሩ አካል የሆኑ ዕቃዎች ሦስተኛ ወገን ዘንድ እንዲቀመጡ፣የሚበላሹ ዕቃዎች እንዲሸጡ፣ወይም ሌላ መጠበቂያ ርምጃ ይጨምራል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት ጉባዔው የዚህን ዓይነት ትዕዛዝ እንዲሰጥ ጥያቄ ያቀረበው ተከራካሪ ወገን ትዕዛዙ ሊያስከትል የሚችለውን ኪሳራ የሚመጥን ዋስትና እንዲያቀርብ ሊያዘው ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት የሚሰጥ ትዕዛዝ እንደአስፈላጊነቱ በፍርድቤት አማካኝነት ሊፈፀም ይችላል፡፡

## 41. ክስ እና የክስ መልስ

1. ከሳሽ ጥያቄውን የሚደግፉለትን ፍሬነገሮች፣ ጭብጦች እና የሚጠይቃቸውን ዳኝነቶች፡-

**ሀ/** በተዋዋዮች ስምምነት በተገለፀው ጊዜ ውስጥ፣ወይም

**ለ/** ተዋዋዮች በመረጡት የግልግል ዳኝነት ማዕከል የሥነሥርዐት ሕግ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ፣ ወይም

**ሐ/** የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ሁለቱም ወገኖችን አስማምቶ ባስቀመጠው ጊዜ ውስጥ፣

መግለፅ አለበት፡፡

2. ተዋዋይ ወገኖች የመልሱ ይዘት ምን መምሰል እንዳለበት ካልተስማሙ በስተቀር፣ ተከሳሽ በክሱ መልክ መልስ አዘጋጅቶ ያቀርባል፡፡

3. ሁለቱም ወገኖች ክሱን ወይም መልሱን ያዳብርልናል የሚሉትን የምስክር ቃልን ጨምሮ ማንኛውም ማስረጃ ማያያዝ ይችላሉ፤ ወይም ወደፊት የሚያቀርቡትን ሰነድ ወይም ማስረጃ በማጣቀሻ ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡

4. በተዋዋይ ወገኖች በሌላ መልኩ ካልተገለፀ በስተቀር፣ እና ጥያቄው በቀረበበት ጊዜ ክርክሩ የሚገኝበትን ደረጃ ከግምት በማስገባት ጉባዔው ተገቢ አይደለም ብሎ ካልከለከለ በስተቀር፣ ማንኛውም ወገን ክሱን ወይም የክስ መልሱን በግልግል ዳኝነት ሂደት ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## 42. የቃልና የጽሑፍ ክርክሮች

1. ተከራካሪ ወገኖች ያደረጉት ስምምነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የቃል ክርክርን የመስማት ወይም ክርክሩን በሰነድ ወይም በሌሎች ግዙፍ ማስረጃዎች ላይ ተመሥርቶ ተገቢውን የማድረግ ሥልጣን የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ይሆናል፡፡

2. የቃል ክርክር የሚካሄድ ሲሆን፣ ስለክርክሩም ሆነ ስለማስረጃ አቀራረቡ እንዲሁም ጉባዔው በጉዳዩ ላይ ስለሚያካሂደው ስብሰባ ለተከራካሪ ወገኖች በቂ የመዘጋጃ ጊዜ የሚሰጥ የቅድሚያ ማስታወቂያ ይሰጣቸዋል፡፡

3. አንዱ ወገን በክርክር ጊዜ ለጉባዔው የሚሰጣቸው መግለጫዎች፣ ሰነዶችና ሌሎች ዓይነት መረጃዎች ሁሉ ለሌላ ተከራካሪ ወገንም ወዲያውኑ ሊደርሱት ይገባል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ጉባዔው ለውሳኔው መሠረት የሚያደርጋቸው የባለሙያ አስተያየት መግለጫዎች ሁሉ ለተከራካሪ ወገኖች ሊደርሱ ይገባል፡፡

## 43. የተከራካሪ ወገን መቅረት

በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ያለበቂ ምክንያት፡-

1. አቤቱታ አቅራቢው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት ክሱን ያላቀረበ እንደሆነ የግልግል ጉባዔው የዳኝነት ሂደቱ እንዲቋረጥ ያደርጋል፡፡
2. ተጠሪው በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት መከላከያውን ያላቀረበ እንደሆነ የግልግል ጉባዔው ተጠሪው የአቤቱታ አቅራቢውን ጥያቄ እንደተቀበለ ሳይቆጥር የዳኝነት ሂደቱን ይቀጥላል፡፡
3. ማንኛውም ተዋዋይ ወገን በአካል ያልቀረበ ወይም ሰነዶችን ያላቀረበ እንደሆነ የግልግል ጉባዔው ዳኝነቱን መቀጠል እና በቀረበለት መረጃ ላይ ተመሥርቶ ውሳኔ መስጠት ይችላል፡፡

## 44. ባለሙያ ስለመሰየም

1. በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የግልግል ዳኝነት ጉባዔ፡-

   ሀ/ በጉባዔው በሚወሰን ጭብጥ ላይ ሙያዊ ማብራሪያ ሊሰጥ የሚችል አንድ ወይም ከዚያ በላይ ሙያተኛ ሊሰይም ይችላል፡፡

**ለ/** ማንኛውም ተዋዋይ ወገን ለሙያተኛው አግባብነት ያለውን መረጃ እንዲሰጥ ወይም ሙያተኛው አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች፣ ዕቃዎች ወይም ሌሎች ንብረቶች እንዲፈትሽ ወይም እንዲመረምር ምቹ ሁኔታን እንዲፈጥር መጠየቅ ይችላል፡፡

2. በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፣ በተዋዋይ ወገኖች በሚቀርብ ጥያቄ ወይም የግልግል ጉባዔው የሙያተኛው መቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው፣

    **ሀ/** ሙያተኛው ሙያዊ ማብራሪያውን በጽሑፍ ወይም በቃል ለጉባዔው ካቀረበ በኋላ በዳኝነት ሂደቱ ላይ ተገኝቶ በተዋዋይ ወገኖች ለሚቀርብ ጥያቄ ምላሽ እንዲሰጥ፣ እና

    **ለ/** በተለየ ጉዳይ ላይ ሙያዊ ምስክርነት ሊሰጡ የሚችሉ ሙያተኞች እንዲቀርቡ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ሊወስን ይችላል፡፡

**45. <u>ማስረጃን ለመቀበል የፍርድ ቤት ድጋፍ</u>**

1. የግልግል ዳኝነት ጉባዔው በራሱ ወይም አንዱ ተከራካሪ ወገን የሚያቀርብለትን ጥያቄ መነሻ በማድረግ፣ ጉባዔው በራሱ ሥልጣን ሊፈፅማቸው የማይችሉ አንዳንድ የማስረጃ ዓይነቶችን መቀበልና የጉባዔውን ትዕዛዝ ማስፈፀም የመሳሰሉ ጉዳዮች በፍርድቤት አማካኝነት እንዲፈፀምለት ጥያቄውን ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጥያቄ የቀረበለት ፍርድ ቤት ጥያቄውን ተቀብሎ በሕግ መሠረት ማስረጃውን ይሰማል፤ ውጤቱንም በጽሑፍ ለግልግል ዳኝነት ጉባዔው ያሳውቃል፡፡

**46. <u>ለግልግል ዳኝነት ጉባዔው የቀረበ ማስረጃን ስለመጠበቅ</u>**

1. ለግልግል ዳኝነት ጉባዔው የቀረበው ማስረጃ የሚጠፋ ወይም ለወደፊቱ የማይገኝ መስሎ የታየ እንደሆነ ተዋዋይ ወገኖች በሚያቀርቡት ጥያቄ ማስረጃው ጥበቃ እንዲደረግለት ጉባዔው ይወስናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ማስረጃው ጥበቃ እንዲደረግለት ከተወሰነ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ማስረጃው ለሚገኝበት ተቋም እና ሥልጣኑ ለሚፈቅድለት ፍርድ ቤት ማስረጃው እንዲጠበቅ ጥያቄ በማቅረብ ያስፈጽማል፡፡

**47. <u>የጉዳዩን ሂደት በጽሑፍ ስለማስፈር</u>**

1. የግልግል ዳኝነት ጉባዔው የክርክሩን ሂደት በጽሑፍ ማስፈር አለበት፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ወይም የግልግል ሂደቱ ተሳታፊዎች ሀሳባቸው ተሟልቶ ካልተጻፈ ወይም ስህተት ያለበት መሆኑን ካመኑ እንዲስተካከል መጠየቅ ይችላሉ፡፡
2. የቀረበው የማስተካከያ ጥያቄ ተቀባይነት ማግኘት አለማግኘቱ በመዝገብ መስፈር አለበት፡፡
3. መዝገቡ በግልግል ዳኞች መፈረም እና ማህተም መደረግ አለበት፡፡ ሆኖም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19/5/ መሠረት ከተቋቋመና የራሱ ማህተም ከሌለው የግልግል ዳኞች ፊርማ ብቻ ይደረግበታል፡፡

## ክፍል ስድስት

## የግልግል ዳኝነት ውሳኔ አሰጣጥ እና የዳኝነት ሂደቱ ስለሚቋረጥበት ሥነ ሥርዓት

### 48. በጉዳዩ ፍሬ ነገር ላይ ተፈፃሚ ስለሚሆኑ ሕጎች

1. አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የግልግል ዳኝነት ጉባዔ ሂደት እና ውሳኔ መሠረት የሚያደርገው ተከራካሪዎች የመረጡትን ሕግ ነው፡፡
2. በስምምነት የተመረጠ ሕግ ከሌለና ሁሉም ተከራካሪዎች የኢትዮጵያ ዜግነት ያላቸው ከሆኑ፣ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው አግባብ ያላቸውን የኢትዮጵያ የፌዴራል እና የክልል ሕጎችን መሠረት በማድረግ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
3. ጉዳዩ ዓለም ዓቀፍ ይዘት ያለው የንግድ ክርክር ሆኖ ባለጉዳዮቹ በሙሉ ወይም በከፊል ኢትዮጵያውያን ያልሆኑ እንደሆነ፣ ጉባዔው የነገሩን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ተፈፃሚውን ሕግ ይወስናል፡፡
4. ተከራካሪዎች በግልጽ ካልፈቀዱ ወይም ተፈፃሚው ሕግ ይህን ለማድረግ ሥልጣን የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ውሳኔውን በሽምግልና መልክ ወይም በርትዕ ሊሰጥ አይችልም፡፡

### 49. ከአንድ በላይ በሆኑ የግልግል ዳኞች ስለሚሰጥ ውሳኔ

በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ የግልግል ዳኞች የሚሰጥ ማንኛውም ውሳኔ የሚሰጠው በድምፅ ብልጫ ነው፡፡ በልዩነት የተሰጠ ሐሳብ ቢኖር ልዩነቱ ይመዘገባል፡፡

### 50. በጋራ ስምምነት አለመግባባትን ስለመፍታት

1. በግልግል ዳኝነት በተያዘው ጉዳይ ላይ ተዋዋይ ወገኖች ዳኝነቱ ከመሰጠቱ አስቀድሞ በሚደርሱት የጋራ መግባባት አለመግባባታቸው የተፈታ እንደሆነ የግልግል ዳኝነት ሂደቱ ይቋረጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ተዋዋይ ወገኖች የደረሱበት ስምምነት በጉባዔው እንዲመዘገብላቸው ጥያቄ ካቀረቡ እና ጥያቄው በጉባዔው ተቀባይነት ካገኘ አለመግባባቱ የተፈታበት ጉዳይ እንደ ግልግል ጉባዔው ውሳኔ ሆኖ በግልግል ጉባዔው መዝገብ ላይ ሊመዘገብ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በጉባዔው የተመዘገበው በጋራ ስምምነት አለመግባባቱ የተፈታበት ውሳኔ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 49 መሠረት እንደተሠጠ ውሳኔ ይቆጠራል፡፡ ውሳኔው በተያዘው ጉዳይ ላይ እንደማንኛውም በጉባዔ የተሰጠ ውሳኔ ሕጋዊ ውጤት ይኖረዋል፡፡

### 51. የግልግል ዳኝነት ውሳኔው ቅርፅ፣ይዘት እና ውጤት

1. የግልግል ዳኝነት ውሳኔው በጽሑፍ ሆኖ በዳኛው ወይም በዳኞቹ መፈረም አለበት፡፡ ከአንድ በላይ ዳኞች በተሰየሙበት የግልግል ጉባዔ የሚሰጥ ውሳኔ በአብላጫው ዳኞች መፈረሙ በቂ ሆኖ ያልፈረመ ዳኛ ቢኖር ምክንያቱ መገለጽ ይኖርበታል፡፡

2. ተዋዋይ ወገኖች ምክንያቱ እንዳይገለጽ ያደረጉት ስምምነት ከሌለ በስተቀር ወይም ውሳኔው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 50 መሠረት በጋራ መግባባት ላይ ተመሥርቶ የተሰጠ ካልሆነ በስተቀር ውሳኔው የተመሠረተበት ምክንያት በግልግል ዳኝነት ጉባዔ መዝገብ መስፈር ይኖርበታል፡፡
3. ውሳኔው የግልግል ጥያቄውን፣ የአለመግባባቱን ፍሬ ነገር፣ ዳኝነቱ የተመሠረተበትን ምክንያት፣የግልግል ዳኝነቱን ወጪ አከፋፈል፣ የተሰጠበትን ቀን እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 37 በተደነገገው መሠረት የግልግል ሥፍራውን መግለጽ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በዳኞች የተፈረመ የውሳኔ ግልባጭ ለእያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ውሳኔው እንዲመዘገብ የሚያስገድድ ሕግ ካለም የውሳኔው አንድ ቅጅ አግባብ ላለው መዝጋቢ አካል እንዲደርስ ይደረጋል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው ቢኖርም፣ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው የዳኝነቱን ሙሉ ክፍያ እና ወጪ በውሳኔው መሠረት እስኪከፈል ድረስ የውሳኔውን ግልባጭ ላልከፈለው ተዋዋይ ወገን እንዲሰጥ አይገደድም፡፡
6. ማንኛውም የግልግል ዳኝነት ጉባዔ የሚሰጠው ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ሕጋዊ ውጤት ይኖረዋል፡፡

**52. <u>የግልግል ዳኝነትን ስለማቋረጥ</u>**

የግልግል ዳኝነት የሚቋረጠው፡-

**ሀ/** ክስ አቅራቢው ክሱን ሲያነሳ ወይም፤

**ለ/** ተዋዋይ ወገኖች ዳኝነቱ እንዲቋረጥ ሲስማሙ ወይም፤

**ሐ/** ሌሎች በሕግ በግልፅ በተደነገጉ ሁኔታዎች

ነው፡፡

**53. <u>ስለማረም፣ መተርጎም እና ተጨማሪ ውሳኔ</u>**

1. በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፣ አንድ ተከራካሪ ወገን የግልግል ዳኝነት ውሳኔ በደረሰው በ 30 (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ፡-

**ሀ/** አንደኛው ተዋዋይ ወገን ለሌላው ተዋዋይ ወገን በማሳወቅ በግልግል ጉባዔው ውሳኔ ላይ የአጻጻፍ ስህተት፣ የቁጥር አጻጻፍ ጉድለት ወይም ያልታሰበና ባለማስተዋል የተዘለለ የቃል ስህተት እንዲታረም መጠየቅ ይችላል፡፡

**ለ/** በተዋዋይ ወገኖች በሚደረግ ስምምነት መሠረት አንደኛው ወገን ለሌላው ተዋዋይ ወገን በማሳወቅ የግልግል ጉባዔው በተለየ የውሳኔው ጭብጥ ወይም ክፍል ላይ ትርጉም እንዲሰጥ መጠየቅ ይችላል፡፡

2. የግልግል ጉባዔው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የቀረበውን ጥያቄ የተቀበለው እንደሆነ ጥያቄውን በተቀበለ በ30 (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ እንደጥያቄው አግባብነት ያርማል ወይም ይተረጉማል፡፡ የሚሰጠው ትርጓሜም የውሳኔው አካል እንደሆነ ይቆጠራል፡፡
3. የግልግል ጉባዔው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) ላይ የተዘረዘሩት ስህተቶች መኖራቸውን ሲረዳ በራሱ ተነሳሽነት ውሳኔው በተሰጠ በ30 (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ ማስተካከል ይችላል፡፡
4. በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር አንደኛው ተዋዋይ ወገን ለሌላኛው ተዋዋይ ወገን በማሳወቅ ውሳኔው በተሰጠ በ30(ሠላሳ) ቀናት ውስጥ ለግልግል ጉባዔው ቀርቦ የተዘለለ የክሱ ክፍል ላይ ተጨማሪ ውሳኔ እንዲሰጥለት የግልግል ጉባዔውን መጠየቅ ይችላል፡፡
5. የግልግል ዳኝነት ጉባዔው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት የቀረበውን ጥያቄ የተቀበለው እንደሆነ በ60 (ስድሳ) ቀናት ውስጥ ተጨማሪ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
6. የግልግል ዳኝነት ጉባዔው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማስተካከያ ለማድረግ፣ትርጓሜ ለመስጠት ወይም ተጨማሪ ውሳኔ ለማስተላለፍ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (5) የተመለከተውን ጊዜ ለተጨማሪ 20 (ሀያ) ቀናት ሊያራዝመው ይችላል፡፡
7. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 51 የተመለከተው የውሳኔ ቅርፅ እና ይዘት ማስተካከያ ለማድረግ ፣ ትርጓሜ ለመስጠት ወይም ተጨማሪ ውሳኔ ለማስተላለፍ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሰባት

## በግልግል ውሳኔ ላይ ስለሚቀርቡ ቅሬታዎች

### 54. የግልግል ውሳኔን ተፈጻሚነት ስለማቆየት

1. በግልግል ስምምነቱ ላይ የይግባኝ መብት ከሌለ ቅሬታ ያለው ወገን የግልግል ዳኝነት ውሳኔው ሳይፈጸም እንዲቆይ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል።
2. ፍርድ ቤት የግልግል ውሳኔ ሳይፈጸም እንዲቆይ ትዕዛዝ መስጠት የሚችለው ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ ሲኖር ብቻ ነው:-
   - ሀ/ ተከራካሪው ወገን የግልግል ስምምነት ለማድረግ የሚያስፈልገው ችሎታ የሌለው እንደሆነ፣ ወይም ስምምነቱ ተፈጻሚ በሚሆነው ሕግ ውጤት የሌለው እንደሆነ፣
   - ለ/ አቤቱታ አቅራቢው ስለግልግል ዳኝነቱ ሂደት በቂ ማስታወቂያ ያልተሰጠው መሆኑን ሲያሳይ ወይም ክርክሩን ለማሰማት አለመቻሉን ሲያስረዳ፣
   - ሐ/ ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ ከግልግል ስምምነቱ የአፈፃፀም ወሰን በላይ ሲሆን፣ ወይም ለግልግል ዳኝነት ጉባዔው ከተሰጠው ሥልጣን በላይ ሲሆን፣
   - መ/ በመሠረታዊ ሕጎች መሠረት ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ በግልግል ዳኝነት ሊታይ የማይችል ሲሆን፣

ሠ/ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው አመሠራረት ወይም ተፈጻሚ የሆነው ሥነ-ሥርዓት ተከራካሪዎቹ ካደረጉት ስምምነት ውጭ ሲሆን፣

3. ፍርድቤት የጉባዔው ውሳኔ እንዳይፈፀም የሚያግደው ተከራካሪው ወገን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩትን ምክንያቶች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ለግልግል ዳኝነት ጉባዔው አቅርቦ የታለፉበት መሆኑን ሲያሳይ ነው።

4. የግልግል ውሳኔ ሳይፈጸም እንዲቆይ ጥያቄ የሚቀርበው ጉዳዩ በግልግል ባይታይ ኖሮ ነገሩን ለማየት የዳኝነት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሆኖ አቤቱታው የሚቀርበውም የግልግል ውሳኔው ለአቤት ባዩ በደረሰ በሠላሳ(30) ቀናት ውስጥ መሆን አለበት።

5. በአቤቱታው ላይ የሚሰጠው ብይን የግልግል ዳኝነት ጉባዔውን የዳኝነት ሥልጣን የማይነካ ከሆነ ወይም የግልግል ስምምነቱን ሕጋዊ ብቃት የማይመለከት ከሆነ ውሳኔው በሙሉ ወይም በከፊል ሳይፈጸም ለማቆየት ትዕዛዝ የሚሰጠው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ወደታየበት የግልግል ዳኝነት ጉባዔ ይመልሰዋል።

**55. ይግባኝ**

1. ተከራካሪዎች በግልግል ስምምነታቸው ይግባኝ አይቀርብበትም ብለው ካልተስማሙ በስተቀር በግልግል ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት ይቻላል።
2. ግልጽ የሆነ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ውሳኔው በሽምግልና መልክ ወይም በርትዕ እንዲወሰን ለጉባዔው ሥልጣን ሰጥተው በዚህ መልክ በተሰጠ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት አይቻልም።
3. በግልግል ውሳኔ ላይ ይግባኝ የሚቀርበው ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት ታይቶ ቢሆን የዚያን ፍርድ ቤት ውሳኔ በይግባኝ ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ነው። ይግባኙ የሚቀርበውም የግልግል ውሳኔው ለይግባኝ ባዩ በደረሰ በስድሳ (60)ቀናት ውስጥ ነው።

**56.የግልግል ውሳኔ ሳይፈጸም ስለማቆየት**

ከተከራካሪዎች ጥያቄ ሲቀርብለት ውሳኔው ሳይፈጸም እንዲቆይ የቀረበውን አቤቱታ ወይም በውሳኔው ላይ የቀረበውን ይግባኝ የሚመለከተው ፍርድ ቤት የግልግል ውሳኔው እንዳይፈጸም የዕግድ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

**57. በሦስተኛ ወገኖች የሚቀርብ መቃወሚያ**

1. በግልግል ዳኝነት ሂደቱ ውስጥ የክርክር ተሳታፊ መሆን ሲገባው ያልተሳተፈና በተሰጠው የግልግል ውሳኔ መብቱ የተነካ ሰው ውሳኔውን በመቃወም ጉዳዩ በግልግል ባይታይ ኖሮ ነገሩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።
2. መቃወሚያውን የሚያቀርበው ሦስተኛ ወገን ከመረጠ አቤቱታውን ጉዳዩን ለተመለከተው የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ማቅረብ ይችላል። ሆኖም አቤቱታውን ለፍርድ ቤት የማቅረብ መብት የማስቀረት ውጤት ይኖረዋል።
3. የግልግል ዳኝነት ጉባዔው የግልግል አበሉንና ሌሎች ኪሳራዎችን በተመለከተ የሚሰጠውን ትዕዛዝ አቤት ባይ ይፈጽማል።
4. መቃወሚያ የሚቀርበው አቤት ባዩ የግልግል ውሳኔው መሰጠቱን ባወቀ በስድሳ (60)ቀናት ውስጥ ሲሆን በማናቸውም መልኩ ቢሆን ውሳኔው ከመፈጸሙ በፊት ሊሆን ይገባል።
5. የመቃወሚያ አቀራረብ ሥርዓቱና ውጤት አግባብ ባላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ይመራል።

## ክፍል ስምንት

## በውጭ ሀገር የተሰጡ የግልግል ውሳኔዎች

### 58. በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ውሳኔ ምንነት እና ሥፍራ

1. ለዚህ ክፍል ዓላማ ሲባል **"በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ውሳኔ"** የሚለው አገላለፅ ከኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውጭ ተከራካሪዎች በመረጡት ወይም ጉዳዩን የተመለከተው የግልግል ጉባዔ በመረጠው ሕግ መሠረት የተሰጠ የግልግል ውሳኔ፣ ወይም በኢትዮጵያ ሕግ ወይም ኢትዮጵያ በፈረመችው አለም ዓቀፍ ስምምነት መሠረት በውጭ ሀገር እንደተሰጠ የሚቆጠር የግልግል ውሳኔን ያካትታል ፡፡

2. አንድ በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ውሳኔ የትም ቦታ ቢፈረም ወይም ከየትም ሥፍራ ወጭ ቢደረግ ወይም በየትኛውም ቦታ ለባለጉዳዮቹ ቢሰጥ በግልግል ስምምነቱ በተመለከተው ወይም የግልግል ዳኝነት ጉባዔው የግልግሉ ቦታ ብሎ በሰየመው ሥፍራ እንደተሰጠ ይቆጠራል፡፡

### 59. በውጭ ሀገር ለተሰጠ የግልግል ውሳኔ ስለሚሰጥ እውቅና

1. አንድ በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ውሳኔ ኢትዮጵያ ውስጥ እውቅና አግኝቶ ተፈፃሚ የሚሆነው ውሳኔው ያረፈበት ጉዳይ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት በግልግል ዳኝነት የሚታይ መሆኑ ሲታወቅ፣ ሀገሪቱ ካፀደቀቻቸው ዓለምዓቀፍ ስምምነቶች እና የሀገሪቱን ፖሊሲ የማይፃረር መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት እውቅና ያገኘ የውጭ ሀገር የግልግል ውሳኔ በሚመለከታቸው ወገኖች ላይ የአስገዳጅነት ውጤት የሚኖረው ሲሆን በማናቸውም ክርክር ወቅት በመከላከያነት ፣ በማቻቻያ መልክ ወይም በሌላ አኳኋን በመከራከሪያነት ሊቀርብ ይችላል፡፡

**60.** **<u>በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ውሳኔን ስለማስረዳት</u>**

1. አንድ በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ውሳኔ እንዲታወቅለት ወይም እንዲፈፀምለት አቤቱታ የሚያቀርብ ወገን ጉዳዩ ለቀረበለት አካል የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ አለበት፡፡

**ሀ/** ትክክለኛነቱ አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ ዋናውን የውሳኔ ሰነድ፣ ወይም በተመሳሳይ አኳኋን የተረጋገጠ ቅጅ፣

**ለ/** ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት እንዲታይ የተደረገበትን ዋናውን የግልግል ስምምነት ወይም የተመሰከረለትን ትክክለኛ ቅጅ ፤

2. የግልግል ውሳኔው የተሰጠበት ቋንቋ ለውሳኔው እውቅና እንዲሰጥ ወይም ውሳኔውን እንዲያስፈፅም አቤቱታ የቀረበለት አካል ከሚሰራበት ቋንቋ የተለየ ቋንቋ ሲሆን አቤቱታ አቅራቢው አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ የውሳኔውን ትርጉም ማቅረብ አለበት፡፡

**61.** **<u>በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ውሳኔ እውቅና እንዳይሰጠው ወይም እንዳይፈፀም ስለመቃወም</u>**

በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ውሳኔ እውቅና እንዳይሰጠው ወይም እንዳይፈፀም የሚቃወም ሰው ውሳኔው በአንቀጽ 54 የተቀመጡትን መመዘኛዎች አለማሟላቱን በማሳየት አቤት ባዩን ሊቃወመው ይችላል፡፡

**62.** **<u>በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ውሳኔን ስለማስፈፀም</u>**

1. በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት እውቅና የተሰጠው የውጭ ሀገር የግልግል ውሳኔ እንደፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ተቆጥሮ በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ 2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ተፈፃሚ ሲደረግ የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸው መረጋገጥ አለበት፡፡

**ሀ/** የተሰጠው ውሳኔ የኢትዮጵያ ሕግ በሚያዘውና በሚፈቅደው ሁኔታ ሊፈፀም የሚችል መሆኑን፣

**ለ/** የግልግል ውሳኔ የተሰጠው የተከራካሪ ወገኖች ለግልግል ጉባዔ ባቀረቡት ስምምነት መሠረት ወይም ውሳኔ የተሰጠበት ሀገር ሕግ በሚፈቅደው መሠረት መሆኑን፤

**ሐ/** ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ዳኞችን ለመምረጥ የእኩልነት መብት ተሰጥቷቸው እንደሆነ ወይም በክርክሩ ላይ ማስረጃቸውን ለማቅረብና ክርክራቸውንም ቀርቦ ለማሰማት የእኩልነት መብት ማግኘታቸውን፤

**መ/** የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ውሳኔው የተሰጠበት ሀገር ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ተቋቁሞ እንደሆነ፤

**ሠ/** ወሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ በኢትዮጵያ ሕግ በግልግል ዳኝነት ሊታይ የሚችል የሆነ እንደሆነና የውሳኔውም አፈፃፀም የሕዝብን ሞራልና ፀጥታ የማይቃረን ከሆነ፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የሚቀርብ የውሳኔ ይፈፀምልኝ ማመልከቻ የሚቀርበው ለፍርድ ቤት ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ዘጠኝ</u>

## <u>የግልግል ዳኝነት ጉባዔ ውሳኔን ስለማስፈጸምና አፈፃፀሙን ስለማገድ</u>

### 63. <u>የግልግል ዳኝነት ጉባዔን ውሳኔ ስለማስፈጸም</u>

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እና የአንቀጽ 54 ወይም 64 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በሀገር ውስጥም ሆነ በየትኛውም ሀገር የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ የተሰጠበትን ሀገር ግምት ውስጥ ሳያስገባ አስገዳጅ እንደሆነ ተቆጥሮ ስልጣኑ ለሚፈቅድለት ፍርድ ቤት በፅሑፍ በሚቀርብ ማመልከቻ በፍትሐብሔር ሥነሥርዐት ሕግ የፍርድ ውሳኔ በሚፈጸምበት አኳኋን ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡
2. የግልግል ዳኝነት ውሳኔ በፍርድ ቤት እንዲፈጸምለት የሚፈልግ ወገን የሚፈጸመው ውሳኔ የተወሰነበት ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የውሳኔ ግልባጭ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ጉዳዩ በውጭ ሀገር የተሰጠ የግልግል ጉባዔ ውሳኔን የሚመለከት ሲሆን በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ስልጣኑ በሚፈቅድለት አካል የተረጋገጠ የውሳኔ ግልባጭ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
3. በኢትዮጵያ በሚገኝ የግልግል ጉባዔ ታይቶ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ በውጭ ሀገር እንዲፈጸም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የፍርድ ባለመብቱ በሚያቀርበው ጥያቄ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፀድቆ ጉዳዩን ለማስፈጸም ሥልጣን ላለው የውጭ ሀገር ፍርድ ቤት ወይም ባለሥልጣን ይላካል፡፡
4. ከማመልከቻው ጋር የሚቀርበው የግልግል ጉባዔ ውሳኔ ግልባጭ የግልግል ዳኝነት ውሳኔው የመጨረሻ መሆኑን ውሳኔውን በሰጠው የግልግል ማዕከል ኃላፊ ከተፈረመ ሸኚ ደብዳቤ ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም የግልግል ዳኝነት ውሳኔ የተሰጠበት ቋንቋ ከአፈጻጸም ፍርድ ቤቱ የስራ ቋንቋ የተለየ ሲሆን አመልካቹ በፍርድ ቤቱ የሥራ ቋንቋ አስተርጉሞ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
6. በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደረገ ልዩ ስምምነት ከሌለ በቀር ፣የውሳኔ ይፈጸምልኝ ማመልከቻ እንደአመቺነቱ ለግልግል ውሳኔ አሰጣጡ መሠረት የሆነው ንብረት በሚገኝበት ወይም የግልግል ጉባዔ ውሳኔው በተሰጠበት ቦታ፣ ወይም የተዋዋይ ወገኖች ነዋሪነት በአንድ አካባቢ ሲሆን በሚኖሩበት ሥፍራ ለሚገኝ እና ጉዳዩ በፍርድ ቤት ቀርቦ ቢታይ ኖሮ ስልጣኑ ላለው ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል፡፡

### 64. <u>አፈፃፀሙን ስለማገድ</u>

1. ከተዋዋይ ወገኖች አንዱ የግልግል ዳኝነት ውሳኔ እንዲፈጸም ቢጠይቅም ሌላኛው ወገን እንዲሻር የጠየቀ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ አፈፃፀሙን ሊያግድ ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የግልግል ዳኝነቱ ውሳኔ እንዲሻር የወሰነ እንደሆነ አፈፃፀሙ ይቋረጣል፤ የግልግል ዳኝነቱ ውሳኔ እንዲሻር የቀረበው ጥያቄ ውድቅ ከተደረገ ፍርድ ቤቱ ውሳኔው እንዲፈፀም ያዛል፡፡

<u>**ክፍል አሥር**</u>

<u>**ስለ ዕርቅ**</u>

**65**. <u>**የእርቅ ሥርዐት አጀማመር**</u>

1. እንታረቅ ባይ ወገን ለዕርቁ መነሻ የሆነውን ጉዳይ በመጥቀስና ምላሽ የሚጠበቅበትን ቀን በመወሰን ለሌላው ወገን የዕርቅ ሓሳቡን በቃል ወይም በጽሁፍ ያሳውቀዋል፡፡
2. የዕርቅ ሓሳቡን ሌላው ወገን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ መቀበሉን የገለፀ እንደሆነ የዕርቅ ሂደቱ ይጀምራል፡፡
3. እንታረቅ ባይ ወገን በ30(ሠላሳ) ቀናት ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት በተወሰነ ሌላ ጊዜ ገደብ ውስጥ ምላሽ ያላገኘ እንደሆነ ሌላኛው ወገን የዕርቅ ሓሳቡን ለመቀበል እንዳልፈለገ በመቁጠር የዕርቅ ሓሳቡን እንዳነሳ ለሌላኛው ወገን ያሳውቀዋል፡፡

**66.** <u>**የአስታራቂዎች ብዛት**</u>

1. ተዋዋይ ወገኖች ሁለት ወይም ከዚያ በላይ አስታራቂዎች እንዲኖሩ በተለየ አኳኋን ካልተስማሙ በቀር የዕርቅ ሂደት በአንድ አስታራቂ ይመራል፡፡
2. የአስታራቂዎች ቁጥር ከአንድ በላይ የሆነ እንደሆነ አስታራቂዎቹ በጋራ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

**67.** <u>**አስታራቂን ስለመሰየም**</u>

1. ተዋዋይ ወገኖች የተለየ ሥነ ሥርዓት እንዲኖር ካልተስማሙ በቀር ፣በአስታራቂ ወይም በአስታራቂዎች ብዛት እና ማንነት ላይ ለመስማማት ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
2. ተዋዋይ ወገኖች በተለይም በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ አስታራቂዎችን ለመሰየም የአንድን ተቋም ወይም የግለሰብ እገዛ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት፡-

**ሀ/** አስታራቂ ሆኖ ለመሥራት ተስማሚ የሆነን ሰው እንዲጠቁሟቸው

ወይም

**ለ/** አስታራቂ ወይም አስታራቂዎችን በቀጥታ እንዲሰይምላቸው

ነው፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት አስታራቂን ለመጠቆም ወይም ለመሰየም ጥያቄ የቀረበለት ተቋም ወይም ግለሰብ አስታራቂን የሚከተሉትን ከግምት ማስገባት አለበት፡-

   **ሀ/** የአስታራቂውን ወይም የአስታራቂዎችን ነፃነት እና ገለልተኛነት እንዲሁም

   **ለ/** እንደ አግባብነቱ፣አስታራቂው ወይም አስታራቂዎቹ ከተዋዋይ ወገኖች የተለየ ዜግነት ያለው ወይም ያላቸው ስለመሆኑ፡፡

4. አስታራቂው ፡-

   **ሀ/** ለአስታራቂነት ሲመረጥ በነፃነቱ እና በገለልተኛነቱ ላይ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ያሳድራሉ ብሎ የሚገምታቸውን ማናቸውንም አካባቢያዊ ሁኔታዎች መግለፅ፣

   **ለ/** በአስታራቂነት ከተሰየመበት ጊዜ አንስቶ በማስታረቁ ሂደት የሚያጋጥሙትን በነፃነቱ እና በገለልተኛነቱ ላይ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ያሳድራሉ ብሎ የሚገምታቸውን ማናቸውንም ሁኔታዎች ሳይዘገይ ለተዋዋይ ወገኖች መግለጽ፣

ይኖርበታል፡፡

## 68. <u>የዕርቅን ጉዳይ ለአስታራቂ ስለማቅረብ</u>

1. አስታራቂው እንደተሰየመ እያንዳንዱ ወገን ስለ ዕርቁ ጉዳይ አጠቃላይ ሁኔታ፣ ባህሪይ እና የዕርቁን ፍሬ ነገር በፅሁፍ እንዲያሳውቁት ሊጠይቅ ይችላል፡፡ እያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን ለአስታራቂው ያቀረበውን ተጨማሪ የፅሁፍ መግለጫ ቅጂ ለሌላው ወገን እንዲደርሰው ማድረግ አለበት፡፡
2. አስታራቂው እያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን አቋሙን እና ይህንኑ ያጠናክሩልኛል የሚላቸውን እውነታዎች በሰነዶች እና በሌሎች ማስረጃዎች አስደግፎ በተጨማሪነት በፅሑፍ እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡
3. አስታራቂው በየትኛውም የዕርቅ ሂደት አግባብነት አላቸው የሚላቸውን ተጨማሪ ማስረጃዎች እንዲቀርቡለት ማንኛውንም ተዋዋይ ወገን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## 69. <u>ዕርቅ በሌሎች ሕጐች እንዲመራ የማይገደድ ስለመሆኑ</u>

ተዋዋይ ወገኖች በተለየ ሁኔታ የሚያደርጉት ስምምነት እንደተጠበቀ ሆኖ ዕርቅ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ወይም በሌሎች ሕጐች መሠረት እንዲመራ አይገደድም፡፡

**70. <u>የአስታራቂው ሚና</u>**

1. አስታራቂው ነፃና ገለልተኛ ሆኖ ተዋዋይ ወገኖች አለመግባባታቸውን በስምምነት እንዲፈቱ ማገዝ አለበት፡፡

2. አስታራቂው ተጨባጭነት ፣ ምክንያታዊነት እና ፍትሐዊነት መርሆዎችን መሠረት አድርጎ በመያዝ የተዋዋይ ወገኖችን መብት እና ግዴታ፤ ልማዳዊ አሠራር እና በተዋዋይ ወገኖች መካከል የነበረውን የቆየ የሥራ ወይም የንግድ ግንኙነት ጨምሮ አለመግባባቱን የሚመለከቱ አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ከግምት ማስገባት አለበት፡፡

3. አስታራቂው የጉዳዩን አካባቢያዊ ሁኔታ በቃል መሰማትን ጨምሮ የተዋዋይ ወገኖች ፍላጎት እና አለመግባባቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ መፍታት አስፈላጊነት ግምት ውስጥ በማስገባት ተስማሚ መስሎ በታየው ሁኔታ ዕርቁን ሊመራ ይችላል፡፡

4. አስታራቂው በየትኛውም የዕርቅ ደረጃ ላይ የዕርቅ ሓሣብ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ የሚቀርበው የዕርቅ ሓሣብ በጽሑፍ እንዲሆን እና ምክንያቱን እንዲገልጽ አይጠበቅበትም፡፡

**71. <u>አስተዳደራዊ ድጋፍ ስለ መጠየቅ</u>**

ዕርቁን ለማመቻቸት ተዋዋይ ወገኖች፣ ወይም አስታራቂው የተዋዋይ ወገኖችን ፈቃድ ሲያገኝ ፣ አግባብነት ካለው ተቋም ወይም ግለሰብ አስተዳዳራዊ ድጋፍ እንዲደረግ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**72. <u>በአስታራቂው እና በተዋዋይ ወገኖች መካከል ስለሚደረግ ግንኙነት</u>**

1. አስታራቂው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከተዋዋይ ወገኖች ጋር በጋራ ወይም በተናጠል የፅሑፍ ወይም የቃል ግንኙነት ሊያደርግ ይችላል፡፡

2. ግንኙነት የሚያደርግበትን ቦታ በሚመለከት በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፣ ከተዋዋይ ወገኖች ጋር በመመካከር እና የዕርቁን አካባቢያዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት አስታራቂው የግንኙነት ቦታውን ይወስናል፡፡

**73. <u>መረጃን ስለመግለጽ</u>**

አስታራቂው ከአንደኛው ተዋዋይ ወገን አለመግባባቱን በሚመለከት ያገኘውን መረጃ ለሌላው ተዋዋይ ወገን ሊገልጽለት ይችላል፡፡ ሆኖም መረጃውን የሰጠው ወገን ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ በምስጢር እንዲያዝለት የጠየቀ እንደሆነ አስታራቂው መረጃውን በምስጢር መያዝ ይኖርበታል፡፡

**74. <u>ተዋዋይ ወገኖች ከአስታራቂው ጋር ሊኖራቸው ስለሚገባ ትብብር</u>**

ተዋዋይ ወገኖች በቅን ልቦና ከአስታራቂው ጋር የመተባበር እና በተለይም በአስታራቂው ሲጠየቁ ሰነዶችን እና ማሰረጃዎችን የመስጠት እንዲሁም በውይይት ጊዜ መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡

**75. <u>በተዋዋይ ወገኖች የሚቀርብ የዕርቅ ሓሳብ</u>**

እያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን በራሱ ተነሳሽነት ወይም ከአስታራቂው በሚቀርብለት ጥያቄ አለመግባባቱን ለመፍታት የሚያስችል አስታራቂ ሓሳብ ማቅረብ ይችላል፡፡

**76. <u>የዕርቅ ስምምነት</u>**

1. አስታራቂው በተዋዋይ ወገኖች ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል የዕርቅ ሓሳብ መኖሩን ሲያምን የማግባቢያ ሰነዱን አዘጋጅቶ ተዋዋይ ወገኖች እንዲያዩት ያደርጋል:: በተዋዋይ ወገኖች ሀሳብ መሠረት የማግባቢያ ሰነዱን ያስተካክላል፡፡
2. ተዋዋይ ወገኖች አለመግባባቱን ለመፍታት ከተስማሙ የዕርቅ ሰነድ በማዘጋጀት መፈራረም ይችላሉ፡፡ አስታራቂው በተዋዋይ ወገኖች ጥያቄ ከቀረበለት፣ የዕርቅ ስምምነት ሰነዱን ራሱ ሊያዘጋጅ ወይም ተዋዋይ ወገኖች የሚያዘጋጁት ከሆነ ሊያግዝ ይችላል፡፡
3. የዕርቅ ስምምነት ሰነዱ በተዋዋይ ወገኖች ሲፈረም በተዋዋይ ወገኖች እና በእነርሱ በኩል የመብት ጥያቄ ባላቸው ሌሎች ሰዎች ላይ የመጨረሻ እና አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡
4. አስታራቂው የዕርቅ ስምምነት ሰነዱን በማረጋገጥ ቅጂውን ለእያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን መስጠት ይኖርበታል፡፡

**77. <u>የዕርቅ ስምምነት ውጤት እና ተፈጻሚነት</u>**

በዚህ አዋጅ ስለ ግልግል ዳኝነት ውሳኔ የሚፈጸምበት ሁኔታ በተደነገገበት አግባብ፣ የዕርቅ ስምምነት ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

**78. <u>ሚስጢራዊነት</u>**

በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ተዋዋይ ወገኖች እና አስታራቂው ከዕርቁ ሂደት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ጉዳዮች በምስጢር መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡ የዕርቅ ስምምነቱን ለማስፈጸም መግለጹ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በቀር የዕርቅ ስምምነቱ ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ ይሆናል፡፡

**79. <u>የዕርቅን ሂደት ስለማቋረጥ</u>**

የዕርቅ ስራ አካሄድ በሚከተሉት ሁኔታዎች ይቋረጣል:-

1. የዕርቅ ስምምነቱ ውሳኔ ተሰጥቶበት በተዋዋይ ወገኖች ሲፈረም፣
2. አስታራቂው ከተዋዋይ ወገኖች ጋር በመመካከር ዕርቅን መቀጠል አላስፈላጊ ሆኖ ማግኘቱን ሲያሳውቅ፣
3. ተዋዋይ ወገኖች ዕርቁ መቋረጡን ለአስታራቂው በጽሑፍ ሲገልፁ፣ ወይም

4. አንዱ ተዋዋይ ወገን ለሌላኛው ተዋዋይ ወገን እና ለአስታራቂው እርቁ ስለማቋረጡ በፅሑፍ ሲገልጽ፡፡

## 80. ወደ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ግልግል ዳኝነት ስለመምራት

አስታራቂው ዕርቅ ስላለመደረጉ በፅሑፍ ካልገለጸ በስተቀር፣ ተዋዋይ ወገኖች በዕርቅ የተያዘውን ጉዳይ ወደ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ግልግል ዳኝነት ማቅረብ አይችሉም፡፡

## 81. የዕርቅ ሥራ አካሄድ ወጪ እና ክፍያ

1. በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ የውል ስምምነት ከሌለ በስተቀር አስታራቂው ለዕርቁ ያወጣውን ወጪ ለመሸፈን ካልሆነ በስተቀር ስለ አገልግሎቱ የሚከፈለው ክፍያ አይኖርም፡፡
2. የዕርቁ ሂደት ሲቋረጥ አስታራቂው የዕርቅ ወጪ በመወሰን ለተዋዋይ ወገኖች በፅሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ወጪ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

    **ሀ/** በአስታራቂው እና በተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ አስታራቂው ለጠራቸው ምስክሮች የሚከፈል ክፍያ እና ወጪ፣

    **ለ/** በተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ በአስታራቂው ጠያቂነት በሙያተኛ ለተሰጠ ሙያዊ የምክር አገልግሎት ወጪ፣

    **ሐ/** በዚህ አዋጅ አንቀጽ 67 ንዑስ አንቀጽ (2) (ለ) እና አንቀጽ 71 መሠረት ለተሰጠ አገልግሎት፣

    **መ/** ሌሎች ከዕርቅ ሥራ አካሄድ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች ወጪዎች እና ክፍያዎች፡፡
4. በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር፣ ወጪዎች እና ክፍያዎች በተዋዋይ ወገኖች በጋራ ይሸፈናሉ፡፡ ሆኖም ወጪው አንደኛውን ተዋዋይ ወገን ብቻ የሚመለከት ከሆነ ወጪው በዚሁ ተዋዋይ ወገን ይሸፈናል፡፡

## 82. ክልከላ

በተዋዋይ ወገኖች የተደረገ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ፡-

1. አስታራቂው በዕርቅ በያዘው ጉዳይ በማንኛውም የግልግል ዳኝነት ወይም የፍርድ ሂደት ላይ ገላጋይ፣ ጠበቃ ወይም ወኪል በመሆን መሥራት ፣
2. በማንኛውም የግልግል ዳኝነት ወይም የፍርድ ሂደት ላይ በተዋዋይ ወገኖች ምስክር ሆኖ መቅረብ ወይም መቆጠር

የተከለከለ ነው፡፡

## 83. በማስረጃነት መቅረብ ስለማይችሉ ጉዳዮች

ተዋዋይ ወገኖች ፡-

1. አለመግባባቱን በዕርቅ ለመፍታት በማሰብ በአንደኛው ተዋዋይ ወገን የተሰጠ አስተያየት ወይም ሓሳብ፣
2. በዕርቅ ሥራው አካሄድ በአንደኛው ተዋዋይ ወገን የተሰጠ የእምነት ቃል፣
3. በአስታራቂው የቀረበ የዕርቅ ሓሳብ፣
4. በአስታራቂው የቀረበውን የዕርቅ ሓሳብ ለመቀበል በአንደኛው ተዋዋይ ወገን የተሰጠ ፈቃደኝነት፣

በግልግል ዳኝነት ወይም በፍርድ ሂደት በማስረጃነት ማቅረብ የተከለከለ ነው፡፡

## ክፍል አስራ አንድ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 84. ስለተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጐች

1. የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፤

**ሀ/** የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ከአንቀጽ 3307 እስከ 3346 ፣ እና

**ለ/** የፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ከአንቀጽ 315-319 እና ከአንቀጽ 350-357

2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

### 85. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 86. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ .....ቀን 2012 ዓ.ም**

**ሳህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**